ኢትዮጵያን አድን ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ በቶሮንቶ

ዓላማ

በኢትዮጵያ ያለው ለውጥ እውነተኛ የህዝብ ለውጥ ሳይሆን የተነሳውን የህዝብ አመጽ በማዳፈን የወያኔን ሰርዓት ለማስቀጠል የተቀነባበር ሴራ መሆኑን በሚዲያ፣ በህዝባዊ ስብሰባ ወዘተ...ማጋለጥ፤

የሀገሪቱን የመበታተን አደጋ ለማስቆምና የህዝባችንንና የሀገራችንን ሁኔታ በማስረጃና በጥናት በተደገፈ ስነድ ለዓለም ሕዝብ ማሳወቅ፣ አደጋውን ለማስቆም የሚቻለውን ሁሉ ማደረግ፤

የጎሳና የዘረኝነት ሰርዓት እንዲያበቃና ህዝባችን በፍቅረና በሰላም እንዲኖር በሀገር ውስጥ የሚደረጉ የህዝብ ንቅናቄዎችን መደገፍ ማገዝ፤

የዘር ማጥፋት ተግባር እንዲካሄድ ያደረጉ፣ የተሳተፉና መመሪያ የሰጡ ወንጀለኞችን ማጋለጥና ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፣ የወያኔ፣ የኦነግ፣ ሻዕቢያ፣ ወንጀለኞችንና አገር የዘረፉ ግለሰቦችን ለፍርድ እንዲቀርቡ
መታገል፤

የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከረበትና ያጸደቀው ሕገ መንግሥት እንዲኖር መታገል፤

ነጻና ገለልተኛ በህዝብ የተመረጡ የምርጫ ቦርድ፣ የህግ አስፈጻሚ አካላት፣ የህዝብ ሚዲያ ወዘተ.. እንዲኖሩ መታገል፤

ከሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት እንዲመሰረት መታገል፤ ሰላም ዲሞክራሲና ፍትህ እንዲሰፍኑ መታገል፤

ተግባር

- በኢትዮጵያዊነት ተሰባስበን የሀገራችንን ሕዝባዊ ትግል በዲፕሎማሲው፣ በገንዘብና በሚዲያ ማገዝ
- ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት በቶሮንቶና አካባቢው ላለው ኢትዮጵያዊ ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኝ ማድረግ
- የተቃውሞ ድምጽ በተለያዩ መንገዶች ማለትም በሰላማዊ ሰልፍ፣ በደብዳቤ ወዘተ ማሰማት
- ለተፈናቀሉና ቤታቸው ፈርሶ ለተበተኑ፣ ለተራቡ ወገኖች በሚቻለው አቅም እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ
- ኢትዮጵያዊያን በአንድነት እንድንቆም ለተለያዩ የሲቪክና የሃይማኖት ክፍሎች ጥሪ ማቅረብ ማስተባበር ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማና ተግባር በስራ ለመተርጎም 'ኢትዮጵያን አድን አስተባባሪ ኮሚቴን' መመስረትና ወደ ስራ መግባት